# አቅራቢ

በፍሩት ኦፍ ሉም እና እህት ኩባንያዎቹ /ኤፍኦቲኤል/፣ የንግድ እንቅስቃሴያችንን በምናከናውንበት ወቅት በንግዱ አለም የሚያስፈልጉ ከፍተኛ የስነምግባር ደንቦች መሰረት ለመስራት እና የአካባቢን እና የሰው ልጆችን መብት ለመጠበቅ በቁርጠኝነት ይሰራሉ። በተመሳሳይ መልኩ ለሁሉም አቅርቦቶች ምርቶቻችንን በምናቀርብበት ወቅት በነዚህ ብቻ ሳይወሰን ለተቋራጮች ፈቃዶች እና ሌሎች የሚመለከታቸው የንግድ አጋሮች /በጥቅል "የአቅራቢዎች" የሚባለውን/ እናከብራለን። ይህ የአቅራቢ የሥነ ሥርዓት ደንብ መለኪያዎች ማለትም አቅራቢዎች መለኪያዎቹን ያሟሉ መሆኑን እና በመርሖዎችን መመራታቸውን ለማረጋገጥ ከዓለም አቀፍ የሠራተኞች ድርጅት መሰረታዊ ስምምነቶች እና ከፍትሃዊ የሠራተኞች ማኅበራት የሥራ ቦታ የሥነ ምግባር መመሪያ ደንብ የተወሰዱ ናቸው።

## ***ሰዎችን ላይ ማዕከል ያደረገ***

<u>ከሰራተኛ ጋር ያለ ግንኙነት:</u> አቅራቢዎች የሰራተኞችን ስራ የሚያከብሩ ደንብ እና መመሪያዎችን ማክበር እና መቀበል አለባቸው። በትንሹ በሀገር እና በአለማቀፍ ደረጃ የተቀመጡ እንዲሁም የማህበራዊ ደህንነት ህጐችን እና መመሪያዎችን መጠበቅ አለባቸው።

<u>ጤና እና ጥንቃቄ:</u> አቅራቢዎች ምቹ እና ጤናማ የስራ ቦታዎችን በማቅረብ አደጋዎችን መከላከል እና አቅራቢዎች ስራቸውን በሚያከናውኑበት ጊዜ የሚያጋጥሙ የስራ ጉዳቶችን መከላከል አለባቸው። አቅራቢዎች ማሟላት ያለባቸው ምቹ ሁኔታዎች የማደሪያ ቦታዎች መስጠት ወይም በአቅራቢዎች የሚመራ የማደሪያ ቦታ ማመቻቸት ምቹ ፣ ንፁህ እና በጥንቃቄ እና በጤና ተያያዥ መመሪያዎች መሰረት የተቀመጡትን ማሟላት አለባቸው። ሰራተኞች ስራቸውን ምቹ በሆነ ሁኔታ እንዲያከናውኑ መሰልጠን እና መሳሪያ ማግኘት አለባቸው።

<u>የህፃናት ጉልበት:</u> አቅራቢዎች የአካባቢውን የት/ቤት እድሜ የሚያስገድዱ ህጐችን እና ህጋዊ የቅጥር እድሜ የተመለከቱትን በመተላለፍ ሰራተኛ መቅጠር አይችሉም። በማንኛውም ሁኔታ አቅራቢዎች ለህፃናት ትወና ወይም ለሞዴል አገልግሎት ማስታወቂያዎችን ወይም ሚዲያን ለመጠቀም ካልሆነ በስተቀር እድሜያቸው 15 አመት ያልሞላቸው ልጆች መቅጠር አይችሉም እንደዚሁም ይህም አስገዳጅ የሆኑ የህፃናት ጉልበት መመሪያዎችን በተጣጣመ ሁኔታ የሚያከብሩ ከሆነ ብቻ ነው።

<u>ጉልበት ብዝበዛ:</u> አቅራቢዎች የሚከተሉትን የጉልበት ብዝበዛዎች ነገር ግን በነዚህ ብቻ ሳይወሰኑ አስሮ ማሰራት ወይም በባርነት በማሰራት ጉልበት ብዝበዛ አያደርጉም። አቅራቢዎች በህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር የሚያመቻቹ ሁኔታዎችን የሚያስቀሩ እርምጃ መውሰዳቸውን ማረጋገጥ እና በንደዚህ አይነት ተግባራት ውስጥ ያሉ ሰንሰለቶችን መቆጣጠር አለባቸው።

<u>ትንኮሣ ወይም ጉዳት:</u> አቅራቢዎች ሁሉንም ሰራተኞች በእኩል መልክ ማክበር እና መያዝ አለባቸው። አቅራቢዎች ማንኛውም ሰራተኛ በአካል በጾታ በስነልቦና ወይም በቃል ወይም በድርጊት እንዲገደድ የሚያደርግ አሰራር እንዳለቸው ማረጋገጥ አለባቸው።

<u>አለማግለል:</u> አቅራቢዎች ሰራተኞችን በሚቀጥሩ፣ ካሳ በሚከፍሉ፣ ማስታወቂያ በሚሰሩ፣ የዲስፒሊን እርምጃ በሚወስዱበት የስራ ውል በሚያቋርጡበት ወይም ጡረታ በሚወጡበት የሰራተኞቹን ጾታ ዘር እምነት፣ እድሜ፣ የአካል ጉዳተኝነት፣የጾታ ግንኙነታቸውን፣ ዜግነቶቻቸውን፣ የማህበር አባል መሆናቸውን፣ የፖሊቲካ አስተያየታቸውን፣ የማህበራዊ ወይም የዘር ምንጫቸውን መሰረት በማድረግ መድሎ አያደርጉም።

<u>የስራ ሰዓት:</u> አቅራቢዎች በህግ ከተፈቀደ ውጪ ሰራተኞች እንዲሰሩ ወይም የትርፍ ሰዓት ስራ እንዲያከናውኑ አያስፈልግም። መደበኛ የሳምንቱ የስራ ሰዓት ከ48 ሰዓት በሚበልጥበት ሰዓት ሰራተኞች በትንሹ 24 ተከታታይ ሰዓት በእያንዳንዱ 7 ቀን ውስጥ ማረፍ አለባቸው። ማንኛቸውም የትርፍ ጊዜ ሰዓት በፍቃደኝነት መሆን አለባቸው። አቅራቢዎች የትርፍ ሰዓት ስራ በመደበኛነት የማይጠይቁ ሲሆን ለትርፍ ሰዓት ክፍያው በውሉ አበል ስሌት መሰረት ካሳ ይከፍላሉ። ልዩ በሆነ ሁኔታዎች ከተጠቀሱት ውጪ የመደበኛ እና የትርፍ ሰአት ብዛት በሳምንት ውስጥ ከ60 ሰዓት መብለጥ የለበትም።

<u>ክፍያ:</u> እያንዳንዱ ሰራተኛ መሰረታዊ ፍላጎቱን የሚያሟላ መደበኛ ደመወዝ የማግኘት መብት ያለው እና ተጨማሪ ገቢ የማግኘት መብት አለው። አቅራቢዎች በትንሹ አነስተኛ የሆነውን ደመወዝ ወይም ተገቢውን በቂ ደመወዝ የሚከፍሉ ሲሆን ይህም ከሁሉም ህጋዊ አስፈላጊ ደመወዞች የሚበልጥ እና ተመጣጣኝ የሆነ በህግ ወይም በውላቸው ላይ የተጠቀሰው ክፍያ ማግኘት አለባቸው። ክፍያው የሰራተኞችን መደበኛ ፍላጎት የማያሟላ እና የተለየ ገቢ የሚሰጥ ከሆነ አቅራቢዎቹ የክፍያውን ሁኔታ በሂደት የሚወስድ እርምጃ ይወስዳሉ።

<u>የመሰብሰብ እና የመደራደር መብት:</u> አቅራቢዎች የሰራተኞችን የመደራጀት እና የመደራደር መብት ማክበር አለባቸው።

## ***<u>ፕላኔትን ታሳቢ ያደረገ</u>***

አቅራቢዎች ስራቸው በአካባቢ ላይ የሚያደርሰውን አሉታዊ ተጽእኖ የሚቀንስ እርምጃ የመውሰድ ሃላፊነት አለባቸው። በትንሹ አቅራቢዎች የሃገር ውስጥ እና ተግባራዊ የሚሆኑ አለም አቀፍ ህጎችን የአካባቢ ሁኔታን ለመጠበቅ የማክበር ግዴታ ያለባቸው ሲሆን ይህም በካይ ቆሻሻዎችን በአግባቡ የማከማቸት እና አነስተኛ የሃይል መጠን ፍጆታ የሚወስዱ የንግድ እንቅስቃሴዎችን ለማከናወን መጣር እና የተፈጥሮ ሃብቶችን መልሶ መጠቀም የሚቻልበትን መንገድ ማመቻቸት አለባቸው።

## ***<u>የምርት ትክክለኛነት</u>***

ሕጎችን ማክበር:- ይህ የሥነ ሥርዓት ደንቦችን ከመጠበቅ በተጨማሪ፣ አቅራቢዎች ሌሎች ሁሉንም ሕጎችን፣ ደንቦች፣ እና ከሥራቸው ጋር የተያያዙትን ስምምነቶችን ማክበር ይጠበቅባቸዋል።

የንግድ ሥነ ምግባሮች፡- ሙስና፣ በኃይል ማስከፈል፣ አደራ በልነት ወይም ምርቱን ወይም የዕቃውን ምንጮች በተሳሳተ መንገድ ማቅረብ በአቅራቢዎች መፈጸም በማንኛውም መንገድ የተከለከለ ነው። ይህም ክልከላ በሚከተሉት ብቻ ሳይወሰን ጉቦ መስጠትም ሆነ መቀበል ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ማመቻቸት እና በተጠየቀ ጊዜ የጥሬ ዕቃውንም ምንጮችን ማሳየት አለመቻልን ያካተተ ነው። እነዚህን ክልከላዎች አቅራቢዎቹ ሊጥሷቸው ኤፍኦቲኤል/FOTL የስራ ግንኙነቱን የሚያቋርጥ እና ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል።

<u>ንዑስ-ተቋራጮች፡</u> አቅራቢዎች ንኡስ-ተቋራጮች የኤፍኦቲኤል/FOTL የፋብሪካ ምርቶች ወይም ይዘቶች ንኡስ-ተቋራጩ በጽኑፍ በስነ ምግባር ደንቡ መስማማቱ ቀድሞ ሳያሳውቅ መጠቀም አይችሉም።

<u>የጉምሩክ ተገዢነት፡</u> አቅራቢዎች ተግባራዊ የሆኑ የጉምሩክ ህጎችና ማክበር እና ምርቶችን በህገ-ወጥ መንገድ እንዳይተላለፉ የሚከለክሉ ፕሮግራሞችን ማስተዋወቅ አለባቸው።

<u>ጥንቃቄ፡</u> አቅቢዎች ያልታወቁ ጭነቶችን (መድሐኒት እና ሌላ ኮንትሮባንዶችን) ለመከላከል አስፈላጊውን የጥንቃቄ ስነስርዓቶች የኤፍኦቲኤል/FOTL ምርቶች በሚዘዋወሩበት ጊዜ ማድረግ ያለባቸው ሲሆን ይህም እነዚህን ሳይጨምር የጉሙሩክ ህግ አጋርነት በጸረ ሽብር ላይ የተቀመጠውን የአሜሪካ የመርከብ ጉዞ መስፈርቶችን ማክበር አለባቸው።

## <u>*አፈጻጸም እና አስገዳጅ ሁኔታ*</u>

<u>የማሳወቅ መስፈርቶች፡</u> አቅራቢዎቹ ይህንን የስነ-ምግባር ደንብ በሚታይ እና ለሰራተኞች ግልጽ በሆነ ሁኔታ መለጠፍ እና ጎብኚዎች እንዲያዩት ማድረግ አለበት (እያንዳንዱ ሠራተኛ፣ ከወጪ በስደት የመጡትንም ሠራተኞችን አካቶ በሚረዱት ቋንቋ ይሆናል)። አቅራቢዎች የስነ-ምግባር ደንቡን ይዘት በተመለከተ በሁሉም ሰራተኞች በየአመቱ የማሳወቅ እና የስልጠና ስራዎችን መስራት አለባቸው።

<u>መዝገብ አያያዝ፡</u> አቅራቢዎች የተሟላ እና ትክክለኛ ምዝገባዎችን የእያንዳንዱ የስነ ምግባር ደንብ ይዘቶችን በተመለከተ ለማረጋገጫ እንዲሆን መያዝ አለባቸው።

<u>የአቅራቢዎች መመሪያ፡ ፈቃድ ያላቸው የማኅበራዊ ቅሬታ አቅረቢ የመምሪያ፡</u> አቅራቢዎች እንደ አስፈላጊነቱ የአቅራቢዎች መመሪያዎችን እና/ወይም ፈቃድ ያላቸውን የማኅበራዊ ቅሬታ አቅራቢ መምሪያዎችን በኤፍኦቲኤል የንግድ ድረ-ገፅ ላይ ዝርዝሩ ስለሚገኝ ይህንኑ ማክበር አለባቸው። www.fotlinc.com

<u>ምዘና እና የማስተካከያ እርምጃ፡</u> FOTL/ኤፍኦቲኤል የውስጥ እንደዚሁም ገልለተኛ የሆኑ ኦዲተሮችን በመጠቀም በቦታው ላይ በመገኘት እና/ወይም ቨርቹዋል በስነ ምግባር ደንቡ መገዛታቸውን ለማረጋገጥ ሊጠቀሙ ይችላሉ። አቅራቢዎች ሙሉ በሙሉ እነዚህን ሁሉ መመዘኛዎች እና እንዲተገበሩ መተባበር እና ዝርዝር የሆነ የቅሬታ መዝገቦች እንዲገኙ ማድረግ አለባቸው። አቅራቢዎች ከFOTL/ኤፍኦቲኤል ጋር በመሆን የማስተካከያ እርምጃዎችን ለመውሰድ የሚያስችሉ በምክንያታዊነት ተገዢነት የሌለባቸው ቦታዎች መከበራቸውን ማረጋገጥ አለባቸው።

<u>ጥሰቶችን ስለ ማሳወቅ፡</u> የስነ ምግባሩ ደንቡ ተጥሷል የሚል ጥርጣሬ በሪፖርት ሲቀርብ ለኤፍኦቲኤል የማህበራዊ ሃላፊነት ክፍል በስልክ +1-270-935-2588 ወይም በኢ-ሜይል code@fotlinc.com ወይም በትክክለኛ የተንቀሳቃሽ ስልክ ዕቃ በመጠቀም ኮዱን ስካን በማድረግ ያሳውቁ። እባክዎን በጥሰቱ ውስጥ ስለተሳተፉት አካላት ወይም የተጣሱ ስምምነቶችን፣ ጉዳይን በቀጥታ ለመፍታት የተወሰዱ እርምጃዎችን፣ እና ምስጥራዊነቱን በጠበቀ መልኩ ስለገጠምዎት ጉዳይ ለእኛ የሚገልጹበትን የመገኛ አድራሻ መረጃን በማካተት ዝርዝር መረጃን ይስጡ። ይህንን የስነ ምግባር ደንብ የሚጥስ ማንኛውም ሰው ወይም እንዲጣስ በማድረግ እገዛ የሚያደርግ ሰው ወይም በማንኛውም ሁኔታ የስነ ምግባር ደንቡ በመጣሱ ላይ የሚደረግ ምርመራ የሚከለክል ሰው በጥብቅ የተከለከለ ነው። ማንኛውም ከላይ የተጠቀሰው መከላከል ለኤፍኦቲኤል ሪፖርት መደረግ አለበት፡

የተከለሰው፣ ፌብሩዋሪ 2022